# በአማራነት መደራጀት-
# ሌላው ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ስልት

ይገረም አለሙ

November 14, 2016

**በቅድሚያ መልእክት፤**

ርእሱን አይተው የጽሁፉን አጠቃላይ መልእክት በጥሞና አንብቦ ለመረዳት ትእግስት በማጣት የጭቃ ጅራፍ ለማጮህ ለሚጣደፉ ወገኖቼ ለሀገር አንድነት፤ለህዝብ አብሮነት፤ ለነጻነት ትግሉና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አንቅፋት እስካልሆነ ድረስ ማናቸውም ሰው በመሰለው መንገድ መደራጀት ሙብቱ መሆኑን የማምን መሆኔን እወቁልኝ ፡፡ ይህች አስተያየቴ መጻፌ በአማራነት ለመደራጀት ለምን አሰባችሁ ለምንስ ሞከራችሁ ሳይሆን በአማራ ይደራጅ ስም የሚነገር የሚጻፈው ኢትዮጵያዊነትን ብቻ ሳይሆን ቆምንለት የምትሉትንም አማራነት የማይጠቅም ሆኖ ስለታየኝ ነው፡

**መንደርደሪያ፤**

ወያኔ በአስራ ሰባት ዓመት አጭር የትጥቅ ትግል ለሥልጣን የበቃው በዘር ተደራጅቶ አማራን በጠላትነት ፈርጆ በመንቀሳቀሱ ነው ብለው ይህን እንደ መልካም ተሞክሮ ወስደው በወያኔ የተጠቃው የእነርሱ ብሄር ብቻ እንደሆነ አድርገው የሚቀስቅሱና የሚደራጁ እንዲሁም አንድ ብሄር ጠላት ፈጥረው ዘረኝነት የሚሰብኩ ሰዎች ከሥልጣን ፍላጎት ቅዠት ያለፈ ሀገራዊ ራዕይ አላቸው ለማለት የሚያበቃ ነገር አይታይባቸውም፡፡ ሊኖራቸውም አይችልም፡፡ ወያኔ ሀያ አምስት አመት ሙሉ ቤተ መንግሥት ተቀምጦ ሀገራዊ ራዕይ መያዝ አይደለም ኢትዮጵያ ሀገራችን ብሎ መጥራትን መለማመድ እንኳን ያልቻለው ከዘረኝነት አስተሳሰብ በመነሳቱ ነው፡፡ ስለሆነም በዘር ተደራጅተን ራሳችንን ከጥቃት ታድገን ወደ ኢትዮጵያዊነት እንሸጋገራለን ወይም እንመለሳለን ማለትመሆን ከመቻሉ አለመቻሉ ነው ሰፊ እድል ያለው፡፡

የዘረኝነት አይነ ርግብ አጥልቀው ሁሉን ነገር በሱ ከተመለከቱ በኋላ አይነ ርግቡን ማውለቅ ይቸግራል፤እንደምንም ማውለቅ ቢቻል ደግሞ አእምሮአቸው ውስጥ ተቀርጾ የቀረው በዘረኝነት አይነ ርግብ የተመለከቱት ነውና ከአይነ ርግቡ መጣል ጋር በአእምሮ ተቀርጾ የተቀመጠው ወጥቶ ሊጣል አይችልም፡፡ የዘረኝነት አረንቋ ሲገቡበት ቀስ በቀስ ነው እስከ ወገብ ከሰመጡበት በኋላ በራስ ጥረትም ሆነ በሌሎች ድግፍ ለመውጣት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ዛሬ በየመድረኩ አንዴ ኢትዮጵያዊ ሌላ ግዜ ደግሞ የጎሳ ፖለቲካ አራማጅ እየሆኑ ሲቸገሩ የምናቸው ለዚህ በቂ ምሳሌ ናቸው፡፡

**በመደራጀት ንትርክ ወቅቱ ነውን!**

ወያኔ ሥልጣኑን ለማስጠበቅ ባወጣው የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ተጠቅሞ በዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለው ኢሰብአዊ ድርጊት ሀያላን የሚባሉትን መንግሥታት፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶችን የመንግሥታቱን ድርጅት ወዘተ በእጅጉ ያሳሰበ ሆኖ ተቃውሞአቸውን እያሰሙ ስጋታቸውን እየገለጹ የሚገኙበት ወቅት ላይ ነን፡፡ እነርሱ እንዲህ በሚያስቡበትና በሚጨነቁበት ወቅት ኢትዮጵያውያን በድርጅትም ሆነ በየግል በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ሽፋን የሚፈጸመውን ኢ.ሰብአዊ ድርጊት ለማስቆምና ለስድስት ወር የታቀደውን ለማጨናገፍ መምከር፣ ማቀድ፣ በተግበር፣ ቀዳሚ ተግባራችን ሊሆን በተገባ ነበር፡፡

ይህ ሊሆን በሚገባበት በዚህ ወቅት ራሳቸውን የአማራ ተወካይ አድርገው በስሙ ድርጅት ሲፈጥሩ የሚያድሩቱ ፖለቲከኛ ነን ባዮች በአንድ በኩል በመደራጀት ጉዳይ ርስ በርሳቸው ሲፋጁ በሌላ በኩል በሀገራዊነት በተደራጁና በተግባር ላይ ባሉት ላይ የቃላት አረራቸውን ሲተኩሱ መስማት የሚሉትን እንዳናምን ብቻ አይደለም ማንነታቸውንና ምንነታቸውን እንድንጠራጠር ያደርጋል፡፡

ለምንድን ነው ይህን የሚያደርጉት? በርግጥ በአማራው ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በእነርሱም ጀርባ ላይ ኖሮ እየቆጠቆጣቸው? አማራው ከወያኔ አገዛዝ መላቀቅ አለበት ብለው አምነው ለዚህ ትግል ራሳቸውን አዘጋጅተውና የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል በቆራጥነት ተነስተው? ለነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ መስጠት አይቻልም፤ይህን የምለው ደግሞ ከተግባራቸው እንዳይባል ሰርተው ያሳዩት ነገር የለምና ከሚሉትና ከሚጽፉት በመነሳት ነው፡፡ለዚህም የሚከተሉትን በአስተውሎት እንመልከት፡፡

**አማራው ራሱን ከጥቃት እንዲከላከል ለማብቃት የድርጅት ብዛት አያስፈልገውም፤**

እንደሚነግሩን በአማራነት ለመደራጀት ምክንያት የሆናቸው እኔ በአልገዛም ባይነቱ የምለው እነርሱ በአማራነቱ የሚሉት በአማራው ላይ የደረሰው በደል ከሆነ በዳዩ ወያኔ ተበዳዩ አማራ ነውና አምስት ስድስት ድርጅት ለመመስረት የሚያበቃ ምንም ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም በየቀኑ ድርጅት እየመሰረቱ ስድስት ነው ሰባት ድርጅት የደረሱት ወገኖች የየራሳቸውን ፍላጎት በዚህ ሽፋን ለማሳካት ያስችለናል በሚል እንጂ በአማራው ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በእነርሱም ጀርባ ላይ ኖሮ እየቆጠቆጠ አላስተኛ ብሏቸው ነው ለማለት አያስችልም፡፡

አማራው በአማራነቱ ብቻ ተበደለ እያሉ የሚተርኩትም ሕዝቡን በቀላሉ ለማነሳሳትና ልክ እንደ ወያኔ ፍላጎታችንን በአጭር ግዜ ለማሳካት ይስችለናል ያሉትን የዘረኝነት መርዝ ለመርጨት እንጂ በርግጥ ለአማራው ነጻነት አስበው ተጨንቀው መሆኑን አያሳም፡፡ እንደሚጽፉትና እንደሚያወሩት አማራ ራሱን ከጥቃት ለመከላከል እንዲችል ለማብቃት ቢሆንማ ኖሮ ጥቂት አማራ ነን ባዮች ብዙ የአማራ ድርጅት መሰረትና ባላሉ ነበር፡፡ ሁሉንም የምናውቃቸው በማህበራዊ መገናኝ ነውና ምን አልባት እንዳንዶች ከሚለጥፉት አርማና ይህንኑ ከሚሰሩ ሁለትና ሶስት ሰዎች ውጪ ሰውም ላይኖራቸው ይችላል፡፡

**አማራውን ከወያኔ አገዛዝ ለማላቀቅ ግንቦት ሰባትና ኢሳት ላይ መዝመት አያስፈልግም፡፡**

ኢሳት በመላው አለም በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እውቅና ያገኘና አድናቆት ያተረፈ በተግባሩም ወያኔን እየተፈታተነ ለመሆኑ ወያኔ ራሱ የመሰከረለት የመገናኛ ብዙኃን ተቋም ነው፡፡ ሀገር ውስጥ እንዳይታይእንዳይሰማ ለማድረግ ወያኔ በቢሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት ማፍሰሱ ከዛም አልፎ ኢሳትና ኦኤም ኤን ላይ በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ እገዳ መጣሉ በዓለም መድረክ ከሚደርስብኝ ፖለቲካዊ ውርደት ኢሳት የሚያደርስብኝ የሥልጣን ማናጋት ይበልጣል ብሎ እንደሆነ ህሊና ያለው ሁሉ የሚገነዘበው ነው፡፡ ግንቦት ሰባትም በአሸባሪነት የተፈረጀውና ኢትፕያ ውስጥ ኮሽ ባለ ቁጥር ከመንግስት ባለሥልጣኖች አፍ የማይጠፋው እየሰራ መሆኑን እንጂ ሀፍረተ ቢሶቹ እንደሚሉት አስመራ መመሸጉን አይደለም የሚመስክረው፡፡ ለሥልጣን በማስጋቱ እንጂ የወያኔ ፍቅረኛ በመሆኑም አይደለም፡፡

ታዲያ በአማራነት ተደራጀን የሚሉን ወገኖቻችን እንዲህ በወያኔ በራሱ በተረጋገጠውና በተፈራው ለወያኔ ሥልጣን አስጊ በሆኑት ኢሳትና ግንቦት ሰባት ተግባር ደስተኛ አለመሆናቸው ከምን የተነሳ ነው፡፡ አሁን ሁለቱም ድርጅቶች በተግባር ከደረሱበት ደረጃና ካተረፉት ህዝባዊ አመኔታ አንጻር ከማህበራዊ መገናኛ ወሬ ያላለፉ ሰዎች ይሉኝታ ቢስ መንፈራገጥ ረሳቸውን ለመላላጥ ይዳርጋቸው ካልሆነ በስተቀር የሚያደርሱት ጉዳት አይታየኝም፡፡ ቢሆንም ግን ጦራቸውን የሰበቁት ኢትዮጵያን ከወያኔ አገዛዝ አላቆ ዴሞክራሲያዊት ሀገር ለማድረግ በተጀመረውና አያሌ ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት በከፈሉበትና አሁንም በየቀኑ መስዋእትነት እየከፈሉበት ባለው ትግል ላይ በመሆኑ በቸልታ የሚታለፍ የትም አይደርሱም ተብሎም በንቀት የሚታይ አይደለም፡፡ እናም መረጃ እየፈለፈሉ የትናንት ማንነታቸውንና የዛሬ ምንነታቸውን እያነፈነፉ በሀቅ ማጋለጥ የሀገር ወዳዶች ግዴት ይሆናል፡፡ ወያኔ የሚፈራውንና የሚጠላውን ተቋም እንዴት የወያኔ ተቀዋሚ ነኝ የሚል በተመሰሳይ ሊፈራውና ሊጠላው ይችላል? እንቆቅልሽ፤

**ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት አዲሱ ስልት**

በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን የሚደረግ ትግል በማንም ተከናወነ በማን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተጠቃሚ ነው፡፡ እኛ የሚመለከተን የአማራ ጉዳይ ብቻ ነው ስለ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መሆን አለመሆን አያገባንም እስከሚል ጽንፍ ቢሄዱ እንኳን አማራው የኢትዮጵያ አካል መሆኑን እስካልካዱ ድረስ አማራውም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተጠቃሚ ነውና በማናቸውም መልክ ከወያኔ አገዛዝ ጋር የሚካሄደውን ትግል የሚያደናቅፉበት ታጋዮችንም የሚነቅፉበት ምክንያት ሊያቀርቡ

አይችሉም፡፡

እዚህ ላይ ሰንደርስ ሁለት ነገር በግልጽ ማየት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ አንደኛው ወያኔ በትግሬ ወካይነት ለቤተ መንግሥት እንደበቃው ሁሉ እኛም በአማራ ወካይነት ለሥልጣን መብቃት እንችላለን ብለው መነሳታቸውን፡፡ ግን ይህን ያሉና የሚሉ ብዙ ሆኑና በየእለቱ አዳዲስ የአማራ ድርጅት መመስረት ሆነ ስራቸው፡፡ ህውኃት ለሥልጣን የበቃው በወቅቱ በትግሬ ስም የተደራጁ ሌሎች ድርጅቶችን ሁሉ በልቶ ብቸኛ የትግራይ ተወካይ ሆኖ ለመውጣት በመቻሉ እንደመሆኑ እነዚህም ተበላልተውም ይሁን ተግባብተው አንድ የአማራ ወካይ ቤተ መንግስቱን አሽጋግሮ የሚያይ ድርጅት እስከሚፈጠር ምጽአት ይደርሳልና የሚያሳዝነው አንዳቸውም ያለሙትን የማያገኙት መሆኑ ነው፡፡ አስተሳሰባቸውን የቀየደው ነገር ይህን እንኳን ለማየት አላስቻላቸውም፡፡

ሁለተኛው በኢሳትና በግንቦት ሰባት ላይ ከያዙት ዘመቻ አንጻር የምንረዳው ጉዳይ ወያኔያዊ ተግባር እየፈጸሙ መሆኑን ነው፡፡ ወያኔ ከመነሻው ኢትዮጵያዊነት አምነትና አስተሳሰብን ለሥልጣኑ አስጊ አድርጎ ማየቱ አከራካሪ አይመስለኝም፡፡ ሊያጠፋው ባይችልም ኢትዮጵያውያን በገነቡት ቤተ መንግስት ተቀምጦ ሀያ አምስት አመት ሙሉ በኢትዮጵያዊነት ላይ መዝመቱ ከዚሁ የተነሳ ነው፡፡አማራው ደግሞ በኢትዮጵያዊነት አቀንቃኝነቱ ይታወቃል፣ በመሆኑም አማራንና ኢትጵያዊነትን ለመለያየት ብዙ ተሰርቷል አልሆነም፡፡ በህውኃት አቃጅነት በብአዴን አስፈጻሚነት ብዙ የተሞከረውና ያልተሳካው የአማራ ብሄረተኝነት ለአማራው ታስቦ ሳይሆን አማራውን ከኢትዮጵያዊነት ለማፋታት ነበር ሳይሆን ቀረ እንጂ፡፡

ይህን ሁሉ ዙሪያ ገብ ሰንቃኝ የአሁኗ አማራው ራሱን ከወያኔ ጥቃት ለመከላከል በማንነቱ መደራጀት አለበት የምትለዋ ዘመቻ ሰሚ አማራን ማደራጀት፤ ወርቋ አማራን ከኢትዮጵያዊነት ማለያየት አጠቃላይ ግቧ አማራው ከኢትዮጵያዊነትም ከአማራነትም ከሁለቱም ሳይሆን ለህገሩም ለራሱም የማይበጅ በማድረግ ወያኔ የፈራውን ሀይል መገላገል ነው፡፡ ከነገሮቹ መረዳት ከወያኔ አድራጎትም መገመት እንደሚቻለው ይህን የሚያደርጉት ዋናዎቹ ጥቂቶች ሲሆኑ እነርሱም አንድም በተለያየ መንገድ ለወያኔ ያደሩ ሁለትም ወያኔ ቀይ ካርድ እያሳየ የሚያስገብራቸው ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ግን ይህን የጀርባ ሴራና ስራ ባለመረዳት በሚያዩትና በሚሰሙት ስሜታቸው እየተጎዳ ሳያውቁ ለሚከተሉዋቸው ደጋፊና ተባባሪ የሆኑ ናቸው፡፡

በአማራው ውስጥ ጥላቻ እንዲስፋፋና ለዚህ የበቃሁት ኢትዮጵያ በማለቴ ነው ብሎ በአማራነት እንዲያስብ ለማድረግ ወያኔ ሆነ ብሎ አስቦና አቅዶ በደሎችን ይፈጽማል፣ለዚሁ ተግባር ተመልምለው ምን አልባትም በቀጥታ ወይ በተዘዋዋሪ ሥልጠና ወስደውና መመሪያ ተሰጥቶአቸው የተሰማሩት ደግሞ የወያኔን ጸረ አማራ ድርጊት እያጎሉ ዘረኛ ቅስቀሳ ያካሂዳሉ፡፡ ከላይ ብዙዎች ያልኩዋቸው በዚህ እየተታለሉም ስሜታቸው እየተጎዳም ስለ አማራነታቸው እንዲያስቡ የተገደዱ ናቸው፡፡

የመጀመሪያዎቹን ከተግባራቸው ማቀብም ሆነ ከወያኔ ማለያየት ከባድ ነው፤ ከተባበርን ግን ማጋለጥና ከዚህ አልፈው እንዳይሄዱ ሌሎችንም እንዳያታልሉ ብሎም ከጨዋታ ውጪ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከሚያዩትና ከሚሰሙት ጀርባ ያለውን ለመረዳት ባለመቻል ወያኔ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ለሚያደርገው ስራ ተባባሪ የሆኑትን ደግሞ መርዳት አስፈላጊም የሚቻልም የሚገባም ነውና ባለማወቅ በጥፋት ላይ የተሰማሩ ወይንም ለአጥፊዎች የሚተባበሩ ወገኖችን የማዳን ስራ እንስራ፡፡